# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር:ገበሬ:ነጋዴ:ወታደር:ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ለ፬ አትም 28.9.67

## ለዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገው ትግል በመፋፋም ላይ ነው::እንገፋበት!

እነዚህ ቃላት በሚፃፉበት ወቅት ቁጥራቸው ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆን ወጣት ተማሪዎችና ዘማች የሰፊው ሕዝብ ልጆች በጊዜያዊው ወታደራዊ መንግስት እስር ቤቶች በመሰቃየት ላይ ናቸው:: ከሁሉ አስቀድመን ለመግለጽ የምንፈልገው አንድ ሃቅ አለ::በአሁኑ ጊዜ 'ተራማጅ ነኝ' በሚለው ደርግ ትእዛዝ ከታሰሩት የሕዝብ ደም መጣጮችና አድሃሪዎች ይልቅ በየጦር ሰፈሩና በየፖሊስ ጣቢያው የሚማቅቁት ተራማጅ የሕዝብ ልጆች ቁጥር እጥፍ ድርብ መሆኑን ነው::

በአድሃሪዎች,ሙሉ ቁጥጥር ስር እየገባ በመሄድ ላይ ያለው ደርግ የስመጥፋውን የሃይለስላሴን ዘመን አፈሳ መጀመሩ ከአስራ አምስት ቀን ወዲህ በከፍተኛ ተቃውሞ እየተፋፋመ የሄደው የሕዝብ ትግል አስጨንቆ እንደያዘው ያሳያል::ይህንን ትግል ለማፈን መጀመሪያ በአፈፀድቅ ፕሮፓጋንዳ ሞከረ::አልሰራም::በየድርጅቱና በየፋብሪካው 'ገለጣ' እያለ ቢዘር መጋለጥ ብቻ እየሆነ አስቸገረው::ከዚያም ማስፈራራት ጀመረ፣ ግራም ቀኝም ሳይለይ ሁሉን 'አድሃሪ' ሁሉን 'አታውቅም ዝም በል' ሁሉን 'የኢትዮጵያ ትቅደም ሰይፍ ይመዘዝብሃል' ሁሉን 'የተኮላ ባህታዊ' እያለ የሰፊውን ሕዝብ ወገን ለመከፋፈል:ጥርጣሬ ለመንዛት:ለማስፈራራት ሞከረ::በዚህ በኩል በያለበት የደረሰበትን ኪሳራ ሁላችንም እናውቀዋለን::አሁን የሕዝቡን ትግል ማወናበድና ማስፈራራት አላገደው ስላለ ተማሪዎችን እያፈሰ ማጉር ጀመረ::አንድ መንግስት አፈፀድቅ ፕሮፓጋንዳውና ማስፈራራቱ አላዋጣህ ብሉት ይህንን የመሰለ ፋሽስታዊ ድርጊት ለመውሰድ ሲገደድ የሕዝብ ትግል አይሎበት መቋቋም እንዳቃተው እንጂ በምንም አይነት ሃይለኝነቱን አያሳይም::

ዛሬ በእስር ቤት የሚማቅቁት እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ያቀረቡቸው ጥያቄዎች ከሰፊው ሕዝብ ጥያቄዎች ተለይተው አይታዩም::ስመጥፋው ሃይለስላሴ እፎ እፎ እስኪለን ድረስ ባሰለቸን አነጋገር ዛሬ በአድሃሪዎች በመጥለቅለቅ ላይ ያለው የአድሃሪዎች ደርግ 'ጥቂት ተማሪዎች' እያለ የሰፊውን ተማሪ ትግል ለማንቋሸሽ ቢሞክር ከራሱ በቀር የሚያታልለው ማንም የለም::የለመድነው:የምናውቀው:የሰለቸን:ያቆ ያለን አነጋገር ነውና::

በመሰረቱ ታጋዮቹ ተማሪዎች ያነሱአቸው ጥያቄዎች የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄዎች ናቸው:: በነዚህ ጥያቄዎች ደግሞ ዛሬ ያልተሰለፈ የሰፊው ሕዝብ ወገን ስለሌለ 90 በመቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሯቸው ነው::ግንቦት 2 ቀን ጠቅላላ ጉባኤውን የፈፀመው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የደርጉን ፀረዴሞክራሲያዊ ድርጊቶች በጥብቅ አውግዞ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች እነዚህ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ እንዲታወቁ ጠይቆአል::ይህ ካልሆነ ደግሞ ያለአንዳች ማወላወል በትግሉ እንደሚገፋ አስታውቋል::በኢትዮጵያ ገጠር ተሰማርተው የሁላችንንም አድናቆት ባተረፈ ቀልጣፋነት ከሕዝቡ ጋር በመዋሃድ ላይ ያሉት ዘማቾች በሙሉ እነዚህ መብቶች ከስራ ላይ እንዲውሉ ጠይቀዋል::ለዚህም በመታገል ላይ ናቸው::ባለፈው የወዝአደሮች ቀን' ወዝአደሩና ጠቅላላው ተራማጅ የተሰለፈባቸው መፈክሮች እነዚህ ሲሆኑ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል:- 'የጽሁፍ የመናገር የመሰብሰብ መብቶች ይሰጡን' 'የሕዝብ ተሳትፍ የሌለበት ሶሻሊዝም የለም' 'ፀረዴሞክራሲያዊ አርምጃዎች ይወገዙ' 'የሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ' የሚሉ ነበሩ::ከዚያም ትግሉ ተፋፍሞ ባለፈው ሳምንት ውስጥ የደርጉ አባሎች 'ገለጣ' እያሉ በየመስሪያ ቤቱ ሲዞሩ የተፋጠጡበትና የተጋለጡበት ይኸው የዴሞክራሲ ጥያቄ ነበር::እግራቸው በረገጠበት መስሪያ ቤት:ፋብሪካ:ድርጅት... በሙሉ ወዝአደሩና ሌሎችም ተራማጆች /የአየር መንገድ ሰራተኞች:የምድር ባቡር:የኮካኮላ ፋብሪካ፡ የፍርድ ሚኒስቴር:የሰራና የመገናኛ:የብሄራዊ ሃብት ልማት:የቴሌኮሙኒኬሽን:የመሬት ይዞታ:የጥጥ ፋብሪካ ...ሰራተኞች/ በያለበት የታገሉት ለነዚህ ጥያቄዎች ነበር::

ባጭሩ ዛሬ ዴሞክራሲ የሰፊው ሕዝብ እንጂ 'የጥቂት ተማሪዎች' ጥያቄ አይደለም::ስለዚህ ትላንት እነ ሃይለስላሴ 'መሬትላራሹን' የጥቂት ተማሪዎች ስራ ይሉ እንደነበረው ዛሬ ይህን የዴሞክራሲ ጥያቄ 'የጥቂት ተማሪዎች' ጥያቄ ለማስመሰል መሞከር ጠርሶ ማወናበድ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ደርጉ አንደሚፎከረው የሰፊውን የኢትዮጵያ ተማሪ ትግል 'አድሃሪ' ብሎ ማስናበትም ከንቱ ሙከራ ነው::ለ15 አመታት ሙሉ የሃይለስላሴን የፕሮፓጋንዳ:የጦርና የፖሊስ ጥይት—ዝናብ ተጋፍጦ:የአስራትና የግርፋት መከራ ተቀብሎ በግንባር ቀደምትነት የተሰለፈውንና በመላ አፍሪካ ወደር የሌለውን ስመጥሩውን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በጥቂት አድሃሪዎች ይመራል ማለት አንደታላቅ ስድብ የምንቆጥረው አነጋገር ነው::አርግጥ ተማሪው ንቅናቄ ውስጥ አንዳንድ ሰርጎገብ አድሃሪዎች መኖራቸው አይካድም::ነገሩ ከመስመር የሚወጣው ራሱ በአድሃሪዎች ባህር አየተጥለቀለቀ በመዋኘት ላይ ያለው ደርግ በተራማጁ የተማሪ ንቅናቄ ባህር ውስጥ ከጠብታ የማያልፉትን አድሃሪ ግለሰቦች የሰፊው ተማሪ ንቅናቄ መልክ ወሳኞች አድርጎ ሲወስዳቸው ነው::ደግሞስ በአሁኑ ጊዜ ከደርጉ ከራሱ አንስቶ አድሃሪዎች የሌሉበት ማን አለ?አንዲያውስ ተማሪውም ሆነ ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚጠይቀው በየመስሪያ ቤቱ አድሃሪ ቢሮክራቶችን ለመፈንቀል፣ በያለበት አድሃሪዎችን አያጋለጠ ከትግሉ ለመነጠል አይደለም አንዴ!የደርጉስ አድሃሪዎች ዛሬ ዲሞክራሲን ከጦር የሚፈሩት ዲሞክራሲ ከታወጀ ተሸፋፍነን ማወናበድ ይቸግርና አንጋለጣለን በለው በመፍራት አይደለም አንዴ! ሰፊው ተማሪና ሰፊው ሕዝብ በአንድ በኩል:አድሃሪ ሃይሎችና ደርጉ በሌላ በኩል ሆነው አየተሰለፉ የሄዱበት ይህ የዲሞክራሲ ጥያቄ ዛሬ ከመጠን በላይ አየከረረና አየተፋፋመ የሚሄድ ለሁለቱም ወገን የሞት ወይም የሽረት ትግል ሆኗል::

በባላገሩ ይህ ጥያቄ ተፋፍሞአል::በዘማቹ:በተራማጅ አስተዳዳሪዎችና በአርሶበሉው የህብረት ተጋድሎ የተነሳ ከደርጉ ቁጥጥር ውጭ አንዳንድ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከስራ ላይ በመዋል ላይ ናቸው::በሕዝቡ ትግል ታልፎ ከሄደ በሃላ ተስተስ ማለት የጀመረው ደርግ ግን ከአድሃሪዎች ጋር በመተባበር ዲሞክራሲን ለማፈን በመፍጨርጨር ላይ ነው::ትግሉ በከረረበት ቦታ ሁሉ ለአድሃሪዎች አያገዘ ተራማጅ አስተዳዳሪዎችን ከስራ ያባርራል::በከፋ:በሃይቆችና ቡታጅራ የምናየው ይህንን ነው::የዘመቻ ጣቢያዎችን አንዳሉ ይዘጋል::በሃረርጌ:በባሌ:በትግራይ:በከፋ የምናየው ይህንን ነው::

በከተማ የሄድን አንደሆነ አስተማሪው:ተማሪው:ወዛደሩ:የመንግስት ሰራተኛው:በጠቅላላው ተራማጁ 'ዲሞክራሲያዊ መብቶች' አያለ ትግሉን አፋፍሞአል::በባላገር አንደሚሆነው ሁሉ በከተማም ደርጉ ፀረዲሞክራሲያዊውን ወገን አየመረጠ በመጋለጥ ላይ ነው::የ5000 ወንድሞቻችንና አህቶቻችን መታፈስ ለዚህ መጋለጥ ቋሚ ምስክር ነው::ኢሰአማን አፍርሶ:የራሱን ሰዎች በየቦታው ከሰካካ በሃላ 'ምርጫ አስደረግሁ' ብሎ በቅምጦቹ የሚመራ ማህበር ለማቋቋም የጠነሰሰው አድሃሪ ሴራ ከሞላጎደል ከሽፎአል::ተራማጁ ወገን ነቅቶ በአንድነት ተነሳስቶ ፋታ ስለነሳው የፈለገውን'ምርጫ' ለማስደረግ አልቻለም::ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ባለማወላወል ባደረጉት ትግል የሰራተኛው ማህበር አንደገና ተከፍቶአል::አድሃሪዎች ዲሞክራሲን ለማፈን የሚያደርጉት ሙከራ ግን አላቋረጠም::ትግሉም በዚሁ አንፃር በመቀጠሉ ደርጉ ከአንግዲህ ያለው ምርጫ ከተማውን በማጥለቅለቅ ላይ ያለውን ይህንን የዲሞክራሲ ጥያቄ አንደጀመረው በሃይል ለማፈን ሞክሮ ከሰፊው ሕዝብ ወገኖች ጨርሶ መቆራረጥና በአድሃሪዎች አጅ ተጠቃሎ መግባት ነው::በዚህም አንደስመጥፋው 'የፀጥታ ኮሚሽን' ተዋርዶ ከታሪክ መድረክ መውረድ፣ ወይም ደግሞ ለዲሞክራሲ ከሚታገሉት ሃይሎች ጎን ተሰልፎ ትግሉን ወደፊት መግፋት ብቻ ነው::መሃል መቆምና በተፋፋመው የመደቦች ትግል በአስታራቂነት መቅረብ የማይቻል ጉዳይ ነው::

ደርጉ በአፍ ብቻ የሰፊው ሕዝብ ወገን ነኝ' አያለ ሲያላዝን አድሃሪ ሃይሎች በከተማም በገጠርም አየተጠናከሩ በመሄድ ላይ ናቸው::ለውጡን በመቃወም ከሸፈቱት አድሃሪዎች ጎን ዛሬ አሊ ሚራህም ተሰልፎአል::የአፋር ሕዝብ ጨቋኝ ገዥ የነበረው ቢትወደድ አሊ ሚራህ ዛሬ ሙሉ በሙሉ ሸፍቶ ከመደብ ወንድሞቹ ተቀላቅሎአል::የአነዚህ አድሃሪ ሃይሎች መጠናከር የርስበርስ ጦርነትን መከፈት በግልጽ ያሳያል::በደርጉ ወላዋይነትና ፀረዲሞክራሲያዊነት ብቻ ሰፊው ሕዝብ ሳይደራጅና ሳይዘጋጅ በዚህ ጦርነት ውስጥ መግባቱ በጣም የሚያሳዝን ነው::የደርጉ ምርጫ ይህ መሆኑ አጅግ አሳፋሪ ነው::

የርጉ የመረጠውን ቢመርጥ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግላቸውን ለመጀመር አሱን አንዳልጠበቁ ሁሉ አሁንም ከሱ ጋር ትግላቸው አያከትምም::ለዲሞክራሲ የሚደረገው ትግል ይፋፋማል አንጂ አያቆምም::ዲሞክራሲ አድሃሪና ተራማጅ መሳዩ ሁሉ በሰፊው ሕዝብ ፊት የሚጋለጥበት:ሕዝቡ የሚማርበትና የሚደራጅበት የትግል መሳሪያ ነው::ይህንን አኛም አናውቀዋለን፣ አድሃሪዎችም:አወናባጆችም:የአዋጅ ሶሻሊስቶችም ያውቁታል::ሰፊው ሕዝብ ይህንን ጥያቄ የሙጥኝ ብሎ የያዘው፣ ጠላቶቹ ደግሞ ከጦር የሚፈሩት በዚሁ የተነሳ ነው::በሁለታችንም በኩል የሞት ወይም የሽረት ጥያቄ ነው፣ የመደቦች ትግል ነው አንግፋበት!

ካለፉት አስራአምስት ቀናት ወዲህ በጠቅላላው በገጠሩ:በየመስሪያ ቤቱ:በየፋብሪካው:በየት/ቤቱና በልዩ ልዩ ማህበራት አየተቀጣጠለ በመፋፋም ላይ ያለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገው ትግል ያለማቋረጥ መግፋት አለበት::በየመስኩ የምንገኝ ተራማጆች በአንድነት ተጋግዘን ካልታገልን ይህንን መብት አዝና የሚወረውርልን የለም::አሁኑኑ ትግላችንን አፋፍመን የአድሃሪዎቹን ሴራ በጊዜው ካላከሸፍነው ሪቮሉሽኑ ወደሃላ የሚወረወርበት ታላቅ አደጋ አለ::ከያለበት:ከመስሪያ ቤት መስሪያ ቤት:ከፋብሪካ ፋብሪካ:ከድርጅት ድርጅት ሃይላችንን አናስተባብር::አድሃሪዎች አንዳይቀድሙን::ፋታ አንስጣቸው!

በያለንበት ተማሪዎች አንዲፈቱ አንጠይቅ
በያለንበት ተራማጆች አንዲፈቱ አንጠይቅ
ለዲሞክራሲያዊ መብቶች ትግሉ ይፋፋም
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል::